# በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ በሰብል ልማትና ጥበቃ ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት

የተዘጋጀ

# የፀረ-ተባይ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሠጣጥ፣ምዝገባ፣አጠቃቀምና ቁጥጥር

# መመሪያ

ታህሳስ 2010 ዓ.ም

አሶሳ

## መግቢያ

ፀረ-ተባይ የሰዉና የእንስሳት በሽታ አስተላላፊዎችን ጨምሮ ማንኛዉንም ተባይ በማከማቻ፣በማጓጓዣ፣በእርሻ ቦታና በቤት ዉስጥ፣በምግብ፣በግብርና ምርቶች፣በእንጨትና የእንጨት ዉጤቶች ወይም የእንስሳት መኖ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም የሚያዉኩ ተፈላጊ ያልሆኑ የእፅዋት /አረም/፣ነፍሳት፣የጀርባ አጥንት ያላቸዉ እንስሳትና ሌሎች በዓይን የማይታዩ ረቂቅ ህዋሳትን ለመከላከል፣ለመቆጣጠር፣ለማጥፋት የሚያገለግሉ ማናቸዉም ንጥረ ነገር፣ድብልቅ ወይም ህይወት ያለዉ ነገር ሲሆን የእፅዋት ዕድገትን ለመቆጣጠር ቅጠሎችን ለማርገፍ፣ ለማድረቅ፣ ፍራፍሬዎች ለማሳሳት ወይም ያለጊዜያቸዉ እንዳይረግፉ ለመከላከል የሚዉል ከምርት ስብሰባ በፊትና በኋላ የምንጠቀምባቸዉን ንጥረ ነገሮችን ሁሉ ያካትታል፡፡

ፀረ-ተባይ መርዝ ስለሆነ በከፍተኛ ጥንቃቄ ስራ ላይ ካልዋለ፣በሰዎች፣በእንስሳት፣በእፅዋት እንዲሁም ደግሞ በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ ስለሆነም ፀረ-ተባይ በሚመረትበት፣በሚከማችበት፣በሚጓጓዝበት ወይም ጥቅም ላይ በሚዉልበት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በፀረ-ተባይ መመረዝ ቅጽበታዊ ወይም ከጊዜ በኋላ ቀስ በቀስ ሊከሰት ይችላል፡፡ ጥንቃቄ በጎደለዉ ሁኔታ ፀረ-ተባይ መጠቀም አካባቢን ከመበከሉም ባሻገር በሰዉና እንስሳት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ በመሆኑም ፀረ-ተባይ በአግባቡ በስራ ላይ ካልዋለ ሊያስከትል የሚችለዉን ጉዳት በመገንዘብ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት የፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 674/2002 ተደንግጓል፡፡ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮዉም ይህንን አዋጅ ለማስፈጽም ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1 የአዉጪዉ ባለሥልጠን**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት የፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 674/2002ን ለማስፈፀም ይህን መመሪያ አዉጥቷል፡፡

**2 አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ "የፀረ-ተባይ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ምዝገባ፣አጠቃቀምና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 11/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**3 ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እስካልተሰጠዉ ድረስ በዚህ መመሪያ ዉስጥ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት አዋጅ ቁጥር 674/2002 ዓ.ም የተጠቀሱ ትርጉሞች እንደተጠበቁ ሆኖ በተጨማሪ፣

"**ቢሮ**" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ ማለት ነዉ፣

"**የሰብል ልማትና ጥበቃ ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ዳሬክቶሬት**"ማለት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት በግብርና ቢሮ የሚገኝ ዳሬክቶሬት ነዉ፣

"**ዞን**"ማለት በክልሉ ዉስጥ ያሉት ግብርና መምሪያዎች ማለት ነዉ፣

"**ወረዳ**" ማለት በዞን ዉስጥ ያሉት ግብርና ጽ/ቤቶች ማለት ነዉ፣

"**ቀበሌ**" ማለት በወረዳ ዉስጥ ያሉት ግብርና ጽ/ቤቶች ማለት ነዉ፣

"**ተባይ**" ማለት በእርሻ ቦታ ወይም በቤት ዉስጥ ምርት ከመመረቱ በፊትና ከተመረተም በኋላ ጥራቱን፣ጣዕሙንና የምግብ ይዘቱን የሚያጎድሉ፣መጠኑን የሚቀንስ፣ለአደጋ የሚያጋልጡ፣የሚጎዱ፣የሚያዉኩ ወይም ጨርሶ የሚያጠፉ ተፈላጊ ያልሆኑ የእፅዋት /አረም/፣ሕይወት ያላቸዉ ነፍሳት፣የጀርባ አጥንት ያላቸዉ እንስሳትና ሌሎች በዓይን የማይታዩ ረቂቅ ህዋሳትን ያጠቃልላል፣

**“ወረርሽኝ ተባይ”** ማለት ከአንድ አካባቢ በመነሳት በአጭር ጊዜ ዉስጥ በፍጥነት በመራባትና ሰፊ ቦታን መሸፈን የሚችል ድንበር ዘለል የሆነና  በዚያዉ አካባቢ ለመከላከል ወይም ለመቆጣጠር እጅግ አስቻጋሪና አዉዳሚ የሆነ ተባይ ማለት ነዉ፣

**“አዲስ ተባይ”** ማለት በአንድ አካባቢ ያልነበረ፣ያልተለመደ፣በቅርብ ጊዜ ከሌላ ቦታ የገባ ወይም የተፈጠረ አደገኛ ተባይ የሆነ ማለት ነዉ፣

**“መደበኛ ተባይ”** ማለት በአንድ አካባቢ የታወቀና የነበረ ድንበር ዘለል ያልሆነና ለመከላከል ወይም ለመቆጣጠር የሚቻል ተባይ ማለት ነዉ፣

“**ፀረ-ተባይ**” ማለት ማንኛቸዉም ዓይነት ተባይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚከላከል፣የሚያባርር፣ወይም የሚገድል የተቀመሙ ንጥረ ነገሮች ዉህደት ወይም በአይን የማይታዩና የፀረ-ተባይን አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ሕይወት ያላቸዉ ነገሮችን ያጠቃልላል፣

**“ፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃቀም**” ማለት ፀረ-ተባይ በአንድ በተወሰነ ቦታ በእፅዋት፣በእንስሳት ወይንም በአፈር ላይ በማስቀመጥ፣በመርጨት ወይንም በማትነን በነፍሳት፣በበሽታ፣በአረምንና በሌሎች ተባይ የሚደርሰዉን ጉዳት ለመከላከል የምንጠቀምበት ዘዴ ነዉ፣

“**የፀረ-ተባይ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**” ማለት በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ማናቸዉም ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት በዘርፉ ለመሰመራት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ያሟሉና ብቁ መሆናቸዉን በማረጋገጥ በቢሮ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማለት ነዉ፣

“**የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወርቀት ምዝገባ**” ማለት ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት ፀረ-ተባይ ለመነገድ በቢሮዉ የተመዘገቡና የብቃት ማረጋገጫ ያወጡትን መመዝገብና ህጋዊ በማድረግ የግል መረጃቸዉን ማደረጀት ማለት ነዉ፣

“**የንግድ ሥራ ፍቃድ**” ማለት በዚህ መመሪያ ዉስጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለተሰጣቸዉ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት አግባብ ባለዉ ህግ መሠረት በክልሉ ንግድ፣ ትራንስፖርትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የሚሰጥ የንግድ ስራ ፍቃድ ነዉ፣

“**ቁጥጥር**” ማለት በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ የተሠማሩት ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት በህጉ- መሠረት መስራታቸዉና የዉስጥ አሰራራቸዉን

የሚፈተሹበት፤ ከህጉ ዉጭ ሆነዉ ሲገኙ እንዲሁም ያለአግባብ በስራዉ በተሰማሩት ላይ የእርምት እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ነዉ፣

“**ተቆጣጠሪ**” ማለት በክልል ግብርና ቢሮ በየደረጃዉ የሚመደቡና የፀረ-ተባይ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ምዝገባን፣አጠቃቀምና ቁጥጥር ስራዉን የሚያካሂዱ ባለሙያዎች ናቸዉ፣

“**የሽያጭ ስፍራ**” ማለት በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የተሠማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት ፀረ-ተባዩን የሚቸረችሩበት ወይም የሚሸጡበት ስፍራ ወይም ቦታ ማለት ነዉ፣

“**ማከማቻ**” ማለት በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የተሠማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት ፀረ-ተባይን ከመሸጫ ቦታ ዉጭ የሚያከማቹበት መጋዘን ማለት ወይም ተቋም ነዉ፣

“**መሸጥ**” ማለት ፀረ-ተባዮን በንግድ ሥርዓቱ ለሽያጭ ለተጠቃሚዉ ማቅረብ ወይንም ለመሸጥ በማሰብ መያዝ ማለት ነዉ፣

“**ስርጭት**” ማለት በክልሉ ዉስጥ በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የተሠማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት ፀረ-ተባዩን ለተጠቃሚዎች፣አርሶ አደሮች ወይም ለአምራች ድርጅቶች በገበያ ንግድ ሥርዓቱ የሚደርሰበት ሂደት ማለት ነዉ፣

“**የታገደ ፀረ-ተባይ**” ማለት በዓለም አቀፍ የተወገዙ፣የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸዉና በሌሎች ምክንያቶች የታገዱ በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ የተሠማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት መጋዘን ዉስጥ ያሉ ወይም ያለአግባብ ወደ ክልሉ የገቡና በሚመለከታቸዉ አግባብነት ባላቸዉ አካላት በህግ የተያዘና ዉሳኔ ያላገኙ ማለት ነዉ፣

“**ጥቅም ላይ ሊዉሉ የማይችሉ ፀረ-ተባይ**” ማለት በባዝል፣በስቶክሆልም ወይም በሮተርዳም ስምምነት መሠረት ከአካባቢና ከጤና አንፀር ጥቅም ላይ እንዳይዉሉ የተገደ ወይም ጥብቅ ገደብ የተጣለበት፣በአያያዝ ጉድለት ወይም ለረዥም ጊዜ ከመከማቸት ምክንያት የተነሳ ይዘቱ የተበላሸ፣ምንጫቸዉ የማይተወቁና ለተለመላት ዓለማ መጠቀም የማይቻል ፀረ-ተባይ ማለት ነዉ፣

“**አደጋ**” ማለት በሰዉ፣በእፅዋት፣በእንስሳት ጤና፣በአካባቢ ወይም በንብረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ወይም ጉዳት ሊያስከትል የሚችል የፀረ-ተባዩ ባህሪይ መለያ ነዉ፣

"ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ሰዉ ወይም በሕግ የሰዉነት መብት የተሠጠዉ አካል ማለት ነዉ፡፡ በዚህ መመሪያ ዉስጥ በወንድ ፆታ የተገለፁት ሁሉ የሴት ፆታንም ያጠቃልላሉ፡፡

## 4. የመመሪያዉ ዓለማ

በቢሮ በህጋዊ መንገድ የፀረ-ተባይ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በማዉጣት በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላካል አገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩትን ግለሰቦች፣ድርጅቶችና ማህበራት ለመከታተል፣ለመደገፍና ለማበረታታት፣በህገ-ወጥ መንገድ በዚህ ስራ ላይ በተሰማሩ አካላት ላይ የእርምት እርምጃ በመዉሰድ ወደ ህጋዊ መንገድ ለማስመለስ፣ነባር የአሠራር ሂደት በማሻሻልና የተጠናከረ በየደረጃዉ ተግባርና ኃላፊነት ግልፅ በሆነ አሠራር በመዘርጋት በሰዉ፣በእፅዋት፣በእንስሳትና በአካባቢ ላይ በፀረ-ተባይ የሚደርሰዉን ጉዳት መቀነስ ነዉ፡፡

## 5. የመመሪያዉ አስፈላጊነት

ግብርናን በማዘመን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የተቀናጀ ተባይ መከላከል ዘዴን መጠቀም በዓለም አቀፍ ደረጃ አመራጭነት የሌለዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በክልላችንም በየጊዜዉ እየተከሰተ ያለዉን የፀረ-ሰብል ተባዮችን ለመከላከል ሲባል የተለያዩ ግለሰቦች፣ድርጅቶችና ማህበራት እንዲሁም በክልሉ በእርሻ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ፀረ-ተባይን የሚጠቀሙ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተዉ ይገኛሉ፡፡

ስለሆነም ከቢሮዉ በህጋዊ መንገድ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በማዉጣት በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩትን ለመከታተል፣ለመደገፍና ለማበረታታት፣በህገ-ወጥ መንገድ በተሰማሩ አካላት ላይ የእርምት እርምጃ ለመዉሰድ የሚያስችል፤እየደረሰ ያለዉን ጉዳት ለመቀነስ አዲስ የአሠራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣ከፀረ-ተባይ ጋር ግንኙነት ያላቸዉን ሌሎች ተግባራት ለመቆጣጠር፣ነባር አሠራርን በማሻሻል የተጠናከረና የተቀናጀ በየደረጃዉ ተግባርና ኃላፊነት ግልፅ አሠራር በመዘርጋት በሰዉ፣እፅዋት፣እንስሳትና በአካባቢ ላይ የሚደርሰዉን ጉዳት ስለሚቀንስ የመመሪያዉ አስፈላጊነት ከፍተኛ ነዉ፡፡

## 6. የተፈፀሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ዉስጥ በሁሉም አካባቢዎች በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ በተሰማሩ፣በፀረ-ተባይ ተጠቃሚ ግለሰቦች፣ድርጅቶችና ማህበራት እንዲሁም በግል እርሻ ስራ ላይ በተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የብቃት ማረጋገጫ፣ የንግድ ፍቃድ አሠጣጥና መሟላት ያለባቸዉ ነገሮች

### አንቀጽ 1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሠጣጥ፡-

ሀ/ አስራ ስምንት /18/ ዓመትና በላይ የሆነ ፀረ-ተባይ ለመሸጥ፣ለማከፋፈል ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልጉ ማንኛዉም ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት ለፀረ-ተባይ ንግድ ሥራ ፍቃድ ቅድመ ሁኔታ የሆነዉን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለባቸዉ፣

ለ/ የፀረ-ተባይ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠዉ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ለዞኖችና ወረዳዎች በዉክልና ሊሰጥ ይችላል፣

ሐ/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በየዓመቱ የሚታደስ ሲሆን ምዝገባዉ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዳበቃ በተመሳሳይ ጊዜ የሚታደስ ሆኖ ለእድሳቱ ዓመታዊ ሪፖርት አሟልቶ የማቅረብ ግዴታ አለበት፣

መ/ የብቃት ማረጋገጫዉ ህጋዊ የሚሆነዉ ለዚህ በተዘጋጀ ዉል ፎርማት ፍቃድ ጠያቂዉና ቢሮዉ ከተፈራረሙ በኋላ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ሲፀድቅ ብቻ ነዉ፣

ሠ/ በክልሉ በመንግስት ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛዉም የመንግስት ሠራተኛ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ማዉጣት አይችሉም፣

ረ/ ሆኖም የመንግስት ሥራዉን ለቆ በዚህ ስራ ላይ መሰማራት ቢፈልጉ የመንግስት ሥራ መልቀቁን የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ ሲያቀርብ ፍቃዱን መዉሰድ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2 የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማዉጣት መሟላት ያለባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች፡-

ሀ/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጠያቂዉ በአካል ቀርቦ በጽሁፍ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠዉ ለወረዳ ወይም ለከተማ አስተዳደር ግብርና ጽ/ቤት ጥያቄ ያቀርባል፣በፍትህ ጽ/ቤት በሚቀርብ የዉክልና ማረጋገጫ ካልሆነ በስተቀር የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ለሌላ ሰዉ መስጠት አይቻልም፣

ለ/ የክልሉ ወይም የአካባቢ ነዋሪ ያልሆነ ፍቃድ ጠያቂ ግለሰብ፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት በየወቅቱ ግንኙነት ሊያደርግና ማንኛዉንም መረጃ ለመስጠት የሚችል በክልሉ ወይም በአካባቢ ቋሚ የሆነ ነዋሪ በፍትህ የፀደቀ ተወካይ ሊኖረዉ ይገባል፤የዉጭ ሃገር ዜጋ ከሆነ ተጨማሪ ፓስፖርት ማቅረብ ግዴታ አለባት፣

ሐ/ የወረዳዉ ወይም ከተማ አስተዳደር ግብርና የሰብል ጥበቃ ባለሙያዎች የቀረበዉን ጥያቄ መርምረዉ ለዚህ በተዘጋጀዉ ፎርም መረጃዉን ሞልቶ ለወረዳዉ ወይም ለከተማ አስተዳደር ግብርና ጽ/ቤቱ ኃላፊ ለማጽደቅ ያቀርባሉ፣

መ/ የወረዳዉ ወይም በከተማዉ አስተዳደር ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ በባለሙያዎች ለማጽደቅ የቀረበለትን መርምሮ ያፀድቃል፣

ሠ/ የወረዳዉ ወይም ከተማ አስተዳደር የሰብል ጥበቃ ባለሙያዎች በወረዳዉ ወይም በከተማዉ አስተዳደር ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ የፀደቀዉን ለክልል ግብርና ቢሮ ይልካሉ፣

ረ/ በአመልካቹ የቀረቡት መረጃዎች ያልተሟሉ ከሆነ ጽ/ቤቱ ለአመልካቹ መረጃዉን እንዲያሟላ በአምስት /5/ የሥራ ቀናት ዉስጥ ያሳዉቃል፡፡ አመልካቹም የተጓደሉትን መረጃዎች በአምስት /5/ የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ አመልካቹ በተጠቀሰዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ መረጃዉን አሟልቶ ካላቀረበ ማመልከቻዉ ተቀባይነት አይኖረዉም፣

ሰ/ የተላከዉ መረጃ በፎርሙ መሠረት የተሟላ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ የሰብል ጥበቃ ባለሙያ ያረጋግጣል፣

ሸ/ የክልሉ ግብርና ቢሮ የሰብል ጥበቃ ባለሙያ መረጃዎችን አጣርቶ የብቃት ማረጋገጫዉን አዘጋጅቶ ለውሳኔ ለሚመለከታቸዉ ኃላፊዎች ያቀርባል፣

ቀ/ ቢሮዉም የቀረበለትን የብቃት ማረጋገጫ መርምሮ ትክክለኘነቱን ከአረጋገጡና ከተፈራረሙ በኂላ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍትህ ቢሮ እንዲያፀድቀዉ ይልካል፣

ተ/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሠጠዉ ማንኛዉም ግለሰብ፣ድርጅት ወይም ማህበራት ከገባዉ ዉል ዉጪ ሰርቶ ቢገኝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ ሰ መሠረት በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 3 የንግድ ስራ ፍቃድ አሠጣጥ፡-**

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለተሰጣቸዉ አካላት አግባብ ባለዉ ህግ መሠረት የንግድ ስራ ፍቃድ የሚሰጠዉ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ንግድ፣ትራንፖርትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ወይም በየደረጃ ባሉ በዘርፉ የሚሠጥ ነዉ፣

ሀ/ **የጅምላ አከፋፋይ ፍቃድ**፡- ከአምራች ድርጅቱ ወይም ፀረ-ተባይ ከሚመረትበት ፋብሪካ ምንም ዓይነት የመያዣ ወይም የፀረ-ተባይ ኬሚካል ለዉጥ ሳያደርግ ባለበት ሁኔታ ለቸርቻሪዎች ወይም ለተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ ለተሠማሩት ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት የሚሰጥ ፍቃድ ነዉ፣

ለ/ **የችርቻሮ ፍቃድ**፡- ከአከፋፋይ የተረከበዉን ፀረ-ተባይ ምንም ዓይነት የመያዣ ወይም የፀረ-ተባይ ኬሚካል ለዉጥ ሳያደርግ ባለበት ሁኔታ ለተጠቃሚ ለሚሸጥ የሚሰጥ ፍቃድ ነዉ፣

ሐ/ **የተባይ መከላከል አገልግሎት ፍቃድ**፡- በቤት ዉስጥ ወይም በእርሻ ሥራ ላይ የሚከሰቱ ተባዮችን ለመከላከል የርጭት ስራ ለማካሄድ ለሚሰማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት የሚሰጥ ፍቃድ ነዉ፣

መ/ ቢሮዉ በተባይ መከላከል አገልግሎት በገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራ መደራጀት ለሚፈልጉ ወጣቶች የአቅም ግንባታ ሥልጠና በመስጠትና በማብቃት ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር እንዲደረጁ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ድጋፍ ያደርጋል፣

ሠ/ በወረርሽኝ ለሚከሰቱ /አይጥ፣ተምች፣የቆላ ፌንጣ፣አንባጣ፣ግሪሳ ወፍና ሌሎች በወረርሽኝ መልክ ለሚከሰቱ አዳዲስ ለሚነሱና በአርሶ አደሩ አቅም ለመቆጣጠር የማይቻሉ ተባዮችን/ ለመከላከል ፀረ-ተባይ ኬሚካልና የሰዉነት መከላከያ ቁሳቁሶች በየደረጃ ባሉ የግብርና መዋቅር ወይም መ/ቤት የማቅረብና የማስቀረብ ግዴታ አለባቸዉ፡፡

**አንቀጽ 4 የንግድ ሥራ ፍቃድ ለማዉጣት መሟላት ያለባቸዉ መስፈርቶች፡-**

### 4.1 ባለሙያዎችን ስለመቅጠር

1. በፀረ-ተባይ ጅምላ አከፋፋይ ወይም ችርቻሮ ንግድ ስራ የሚሰማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት ለዚሁ ስራ አንድ የሙያ ወይም ቴክኒክ ድጋፍ የሚሰጥ ባለሙያ መቅጠር ግዴታ አለባቸዉ፣
2. ባለሙያዉ በእፅዋት ጥበቃ፣እፅዋት ሳይንስ፣አጠቃላይ እርሻ፣ኬሚስትሪ፣አፕላይድ ኬሚስትሪ፣ባዮሎጅ ትምህርት ዘርፍ ቢያንስ በዲፕሎማ የተመረቀ ከአራት /4/ ዓመት የስራ ልምድ ያላነሰ፣በመጀመሪያ ድግሪ የተመረቀ ከሁለት /2/ ዓመት የስራ ልምድ ያላነሰ፣በሁለተኛ ድግሪ የተመረቀ ዜሮ /0/ ዓመት የስራ ልምድ ያለዉ መሆን ይኖርበታል፣
3. በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ የሚሰማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ አንድ ከተራ ቁጥር 2 ላይ የተቀመጡትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ከሆኑ በራሳቸዉ የሽያጭና የተባይ መከላከል አገልግሎቱን ስራ መስጠት ይችላሉ፣
4. የሚቀጠረዉ ባለሙያ በፀረ-ተባይ አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም በፀረ-ተባይ ምክንያት ሊደርስ የሚችለዉን ጉዳት ለመከላከል አስፈላጊዉን ምክር አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን የቅጥር ስምምነቱ የመንግስት ደንብና መመሪያን መሠረት ያደረገና በዉልና ማስረጃ ፀድቆ የቀረበ መሆን ይሮርበታል፣
5. በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላካል አገልግሎት ስራ ላይ የሚሠማሩ ዩኒዬኖችና መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የማከማቻና የመሸጫ ሱቃቸዉን ከምግብ፣መጣጥ፣ ዘርና ማዳባሪያ ጋር ማከማቸት በፍፁም አይቻልም፡፡ ሌሎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4.2፣4.3፣4.4፣4.5 እና 4.6 የተጠቀሱት የመተግባር ግዴታ አለባቸዉ፡፡

### 4.2 የሰዉነት መከላከያ ትጥቅ

4.2.1.ማናኛዉም በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ወይም አገልግሎት ሰጪ ግለሰቦችና ማህበራት በዚህ መመሪያ ከፀረ-ተባይ ጋር የተያያዙ ገደቦችን በሚቃረን መልኩ ፀረ-ተባይን መጠቀም ወይም ሠራተኞቻችዉ እንዲጠቀሙ ማድረግ ወይም ሌላ ሰዉ እንዲጠቀም ሃሳብ ማቅረብ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት አዋጅ ቁጥር 674/2002 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 3 /ሐ/ መሠረት በህግ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

4.2..2. ማንኛዉም በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የተሰማራዉ አካል አሠሪ ሠራተኛዉን ፀረ-ተባይ እንዲጠቀም ሲያደርግ ወይም ሲፈቅድ ፀረ-ተባዩን በጥንቃቄ መያዝ የሚያስችሉ አስፈላጊ የስልጠና፣የሰዉነት መከላከያ ትጥቆችንና የአሠራር መመሪያዎችን በማቅረብ ሠራተኛዉ

እነዚህን እንዲጠቀም ማድረግ ግዴታ አለበት። ይህን ሳያደርግ በሠራተኛዉ ላይ ጉዳት ቢደርስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ ሰ እና ሸ መሠረት አሠሪዉ የህክምና ሙሉ ወጪዉንና የጉዳት ካሳ መክፈል ግዴታ አለበት።

4.2.3. ማንኛዉም አሠሪ ሠራተኛዉን ከፀረ-ተባይ ጋር በተገናኘ ሁኔታ እንዲሠራ ሲያደርግ፡-

ሀ/ ከፀረ-ተባይ ጋር በተገናኘ ሠራተኛዉን ስራዉ በብቃት ለመስራት የሚያስችለዉ ባቂ የስልጠናና ሌሎች የአሠራር መመሪያዎች እንዲያገኝ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

ለ/ አሠሪዉ ግለሰብ፣ድርጅት ወይም ማህበራት በየስድስት /6/ ወር ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከዚህም በአነሰ ጊዜ ሠራተኛዉ ወይም ግለሰቡ መመርመር በሚያስፈልግበት ወቅት አሠሪዉ አካል ወይም ድርጅት የሕክምና ምርመራ እንዲያገኝ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

ሐ/ አሠሪዉ ግለሰብ፣ድርጅት ወይም ማህበራት ለባለሙያዉ የሚያስፈልጉ የሰዉነት መጠገኛ ምግቦችና ሌሎች የንጽህና መጠበቂያና ሌሎች ተያያዥ ቁሳቁሶችን የማቅረብ ግዴታ አለበት፣

መ/ ማንኛዉም በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ የተሠማራ አካል በንክኪ ወይም በትነት የሚደርሰዉን ጉዳት ለመከላከል ሙሉ የሰዉነት መከላከያ ትጥቅ ማለትም  ቱታ፣ቦት ጫማ፣የእጅ ጓንት የዓይን መነፅር፣የአፍና አፍንጫ መከላከያ ማስክንና የኬሚካል ማቀናነሻዎችን ያጠቃልላል፣

ሠ/ በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛዉም ግለሰብ፣ድርጅት፣ማህበራት ያለምንም ተጨማሪ ፍቃድ ሙሉ የሰዉነት መከላከያ ትጥቆችንና ሌሎች መርጫ መሳሪያዎችን ማቅረብ ይችላሉ፣

ረ/ በአንቀጽ 3 ፊደል መ ላይ ከተጠቀሱት ዉጭ ሌሎች መደበኛ ተባዮችን ለመከላከል የግል ባለሀብቶችና አርሶ አደሮች ሙሉ የሰዉነት መከላከያ ትጥቆችንና ሌሎች መርጫ መሳሪያዎችን ሊኖራቸዉ ይገባቸዋል።

### 4.3 የተባይ መከላከያ አገልግሎት

በቤት ዉስጥ ወይም በእርሻ ላይ የሚከሰቱ ተባዮችን ለመከላከል በተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ የሚሰማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት ለርጭት አገልግሎት የሚዉሉ

ቁሳቁሶችንና መከላከያ ትጥቆችን አሟልተዉ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህን ቁሳቁሶች ካላሟሉ በተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ መሰማራት አይችሉም፡፡

4.4 መጋዘን

ሀ/ በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የሚሰማራ ግለሰብ ወይም ድርጅት የራሱን የማከማቻ መጋዘን በግሉ የተዘጋጀ ወይም በኪራይ ሊሆን የሚችል ማዘጋጀት ያለበት ሲሆን ለዚሁ ማስረጃ የቤት ኪራይ ዉል ማቅረብ ይኖርበታል፣

ለ/ በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ የሚሰመራ ግለሰብ፣ድርጅት፣ማህበራት የማከማቻ መጋዘኑን አቅጣጫ የሚያሳይ ወይም የማስጠንቀቂያ

ምልክት ታፔላ ግልጽ በሆነና በሚታይ ቦታ መትከል/ማቆም ይኖርበታል፣

ሐ/ በፀረ-ተባይ ጅምላ አከፋፋይ አቅራቢነት ስራ ላይ የሚሰመራ ግለሰብ፣ድርጅት ወይም ማህበራት የማከማቻ መጋዘን ከከተማ ክልል አንድ ኪሎ ሜትር ማራቅ አለበት፣

መ/ የፀረ-ተባይ መጋዘን ለመኖሪያነት የተሰራ ቤት ወይም ለመከራየት የተሰሩ ዶርሞች ክፍል መሆን አይችልም፡፡ መጋዘኑ በግንብ የተሰራ ሆኖ ቢያንስ ከ50 ካሬ ሜትር ማነስ የለበትም፣ ሆኖም በተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ የሚሰማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች መጠኑ ከ25 ካሬ ሜትር መጋዘን ሊኖራቸዉ የሚችል ሆኖ ወለሉ ከሊሾ የተሠራ መሆን ይገባል፣

ሠ/ መጋዘኑ ከመኖሪያ ቤት፣ከገበያ ቦታዎች፣ከትምህርት ቤቶች፣ከሆስፒታሎች፣ከህፃናት መዋያ ቦታዎች፣ከምግብና መጠጥ ቤቶች፣ከመናፈሻዎች፣ከወንዝና ከኩሬዎች ከ100 ሜትር በላይ የራቀና ለአደጋ መንስኤ ያልተጋለጠ መሆን ይኖርበታል፣

ረ/ የመጋዘኑ የበር ስፋት ከ3 ሜትር፣ቁመቱ ከ2 ሜትር ያላነሰ ሆኖ አየር በበቂ ሁኔታ መዘዋወር እንዲችል በቂ መስኮቶች ሊኖረዉ ይገባል፡፡ የጣሪያ ርዝመት ከ3 ሜትር በላይ የሆነ መሆን ይኖርበታል፣

ሸ/ በመጋዘኑ ግቢ ዉስጥ ለጥበቃ የተለየ ክፍል፣ለሠራተኞች ንጽህና መጠበቂያ ዉሃ፣መፀዳጃ ቤትና መብራት ያለዉ፣ የእሳት አደጋ ማጥፊያ የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ያለዉ ሆኖ በማከማቻ መጋዘን ዉስጥ ምግብና መጠጥ እንዲሁም ዘርና ማዳባሪያ ማከማቸት በፍፁም አይቻልም፡፡

## 4.5 የፀረ-ተባይ መሸጫ ሱቅ

ሀ/ በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የሚሰመራ ግለሰብ፣ድርጅት ወይም ማህበራት የራሱን የመሸጫ ሱቅ በግሉ ወይም በኪራይ የተዘጋጀ ሊሆን የሚችል ሲሆን ለዚሁ የኪራይ ዉል ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፣የማከማቻ መሸጫ ሱቁን አቅጣጫ የሚያሳይ ታፔላ ግልጽ በሆነና በሚታይ ቦታ መትከል/ማቆም ይኖርበታል፣የፀረ-ተባይ የመሸጫ ሱቅ ለመኖሪያነት የተሰራ ቤት ወይም ዶርሞች መሆን አይችልም፣

ለ/ የመሸጫ ሱቁ ከመኖሪያ ቤት፣ከገበያ፣ከትምህርት ቤቶች፣ከሆስፒታሎች፣ከህፃናት መዋያ ቦታዎች፣ከምግብና መጠጥ ቤቶች፣ከመናፈሻዎች፣ከወንዝና ከኩሬዎች ከ50 ሜትር በላይ የራቀና ለአደጋ መንስኤ ያልተጋለጠ መሆን ይኖርበታል፣በሱቁ ዉስጥ ምግብና መጣጥ እንዲሁም ዘርና ማዳባሪያ ማከማቸት በፍፁም አይቻልም፡፡

ሐ/ ተጠቃሚዎች ፀረ-ተባዩን በሚፈልጉት መጠንና ጊዜ እንዲያገኙ የመሸጫ ሱቁ በየቀኑ ክፍት መሆን አለበት፣

## 4.6 የተሸጠ ፀረ-ተባይ መረጃ አያያዝ

ሀ/ ማንኛዉም በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የሚሰማራ ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም ማህበራት በእጁ የገቡ ፀረ-ተባይዮችን የተከፋፈለዉን መጠን፣ለማን እንደተከፋፈለ፣በችርቻሮ የተሸጠ ከሆነ ዓይነቱ፣መጠኑ የተሸጠበት ጊዜ የተሸጠለት ድርጅት ወይም ግለሰብ ስም እንዲሁም በርጭት አገልግሎት አሠጣጥ ለተሠማሩ ግለሰብ፣ ድርጅት፣ማህበራት ወይም ቡድኖች የተካሄደ ከሆነ ዬት፣መቼ፣ለምን ዓይነት ተባይና ተባዩ ያለባት የዕድገት ደረጃ ፣በስንት ሰዓትና የአካባቢዉ የአየር ሁኔታ፣ርጭቱን ያከናወነዉ ባለሙያ ስምና የመሳሰሉት መረጃዎችን የሚገልፅ መዝገብ በማዘጋጀት በየወቅቱ በመዝገቡ ላይ መመዝገብ ይጠበቅበታል፣

ለ/ መረጃዉን ተቆጣጣሪዉ ቁጥጥር በሚያከናዉንበት ወቅት ወይም በየዓመቱ እድሳት ሲካሄድ ይመረምራል፡፡

# ክፍል ሦስት

## ፀረ-ተባይ መለያ መሟላት ያለበቸዉ ነገሮች

### አንቀጽ 5 ፀረ-ተባይ መለያ መስፈርቶች፡-

የፀረ-ተባይ መለያ የሚከተሉትን መስፈርቶች መሟላት አለባቸዉ፡፡ በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ፅሑፍ በዘለቄታዉ ጉልቶ እንዲታይ ሆኖ ከማሸጊያ ጋር የተያዘና የሚከተሉትን ነጥቦች የካተተ መለያ ሊደረግለት ይገባል፡፡

1. የፀረ-ተባዩ ስም፣
2. የዓለም የእርሻና የጤና ጥበቃ ድርጅት /FAO and WHO/ በተወሰነዉ መደብ መሠረት አደገኛነቱን የሚያስጠነቅቅ የጽሑፍና ስዕላዊ መግለጫ፣
3. የዋናዉን ንጥረ ነገር የወል ወይም የንግድ መጠሪያ እና የድብልቅ መጠን የሚያሳይ መግለጫ፣
4. ፀረ-ተባዩ ሲመረት የተሰጠዉን መለያ ቁጥር፣
5. አጠቃቀሙን የሚገልፅ ጽሑፍ፣
6. ፀረ-ተባዩ ከተመረተ በኋላ አደጋ እንዳያስከትል መቆየት የሚያስፈልግበት ጊዜ፣ቦታና የተመረተበት እና አገልግሎቱ የሚያበቃበት ዓመተ ምህረት ያካተተ መሆን ይገባል፡፡

# ክፍል አራት

## የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ስለማገድ፣ስለመሰረዝና ስለማጓጓዝ

### አንቀጽ 6 የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ፡-

**6.1 የክልሉ ግብርና ቢሮ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በአንዱ ምክንያት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወርቀቱን ያግዳል ወይም ይሰርዛል፡-**

1. በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ሥራ ላይ የተሠመሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት በየወቅቱ የብቃት ማረጋገጫን የማደስ ግዴታ አለባቸዉ፡፡ በየዓመቱ የማያድሱና የማሳደሻ ጊዜ ለአንድ ዓመት ያሳለፉ ሁለት ሺህ /2,000/ ብር፣ለሁለት ዓመት ያሳለፉ አምስት ሺህ /5,000/ ብር የሚቀጡ ሲሆን፣ለሦስተኛ ዓመት ያሳለፉ የብቃት ማረጋገጫዉ ተሰርዞ የንግድ ስራ ፍቃዳቸዉ እንዲሰረዝ ለክልሉ ንግድ፣ትራንስፖርትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በደብዳቤ ያሳዉቃል፣
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ፍቃድ ለማግኘት በማታለል፣የሀሰት ማስረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ መሆኑ ሲታወቅ፣
3. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወርቀቱን ፍቃድ ከተሰጠባቸዉ ዝርዝር ሁኔታዎች ዉጪ ለሌላ ተግባር ሲጠቀምበት ሲገኝ ቢሮዉ የምስክር ወርቀቱን ሊያግደዉ ወይም ሊሰርዘዉ ይቻላል፡፡ ከተሠጠዉ ህግ-ዉጪ ተጠቅሞ የተገኘ ግለሰብ ወይም ድርጅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 በህግ ይጠየቃል፣
4. ግለሰቡ፣ድርጅቱ ወይም ማህበራት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሌለዉና ህጋዊ መስፈርቱን ሳያሟላ በተቀጠረ ባለሙያ ስራዉን ሲያሰራ ወይም ሲሰራ ከተደረሰበት፣እንዲሁም በመመሪያዉ መሠረት ፍቃድ እንዳያገኙ ከተከለከሉ ግለሰቦች በአባልነት /በባለቤትነት/ መኖራቸዉ ከተረጋገጠ፣
5. የቁጥጥሩ ስራ ሲካሄድ ግለሰቡ፣ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ለማስመርመር ፍቃደኛ ሳይሆኑና የተጠየቁትን መረጃ ካልሰጡ፣
6. እንዲያስተካክል ማስጠንቃቂያ ተሰጥቶት በተሰጠዉን የጊዜ ገደብ ዉስጥ አጠናቆ ካላቀረበ፣
7. ከላይ ከተራ ቁጥር 1-6 በተዘረዘሩት ነጥቦች በአንዳቸዉ ብቻ የክልሉ ግብርና ቢሮ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ይሰርዝና የንግድ ስራ ፍቃዱ እንዲሰረዝ ለፍቃድ ሰጪዉ አካል በፅሑፍ ያሳዉቃል፡፡

### 6.2 የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ለመሰረዝ መከተል ያለባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች፡-

ሀ/ ምዝገባዉን ከመሰረዙ በፊት ድርጅቱ፣ግለሰቡ ወይም ማህበሩ የምዝገባዉን መሰረዝ የሚቃወም ከሆነ በአስራ አምስት /15/ የሥራ ቀናት ዉስጥ ምክንያቱን በጹሑፍ እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል፣

ለ/ ድርጅቱ፣ግለሰቡ ወይም ማህበሩ ምክንያቱን በጹሁፍ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በአስር /10/ የሥራ ቀናት ዉስጥ የክልሉ ግብርና ቢሮ ዉሳኔዉን ለድርጅቱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

ሐ/ ቢሮዉ ዉሳኔ እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ ግለሰቡ፣ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ታግዶ ይቆያል፣

መ/ ምዝገባዉ ሲሰረዝ ድርጅቱ፣ግለሰቡ ወይም ማህበሩ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ለክልል ግብርና ቢሮ የመመለስ ግዴታ አለበት፣

ሠ/ የብቃት ማረጋገጫዉ ሲሰረዝ ቢሮዉ በሰዉ፣እንስሳት ወይም እፅዋት ጤናና በአካባቢ ላይ ሊደርስ የሚችለዉን ጉዳት ለመከላከል ፀረ-ተባዩ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፣

ረ/ እንዲሰበሰብ የተወሰነዉ ፀረ-ተባይ በእጁ የሚገኙ ማንኛዉም በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካል ዉሳኔዉ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ በአስር /10/ የሥራ ቀናት ዉስጥ ለክልሉ ግብርና ቢሮ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፣

ሰ/ በክልሉ ግብርና ቢሮና በየደረጃ ባሉ መዋቅሮች፣ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት መካከል ፀረ-ተባይን በተመከለተ በየጊዜዉ በሚቀርቡ ሪፖርቶች፣በስልክና በአካል የመረጃ ልዉዉጥ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 7 ፀረ-ተባይን ማጓጓዝ፡-**

ማንኛዉም ሰዉ ጥብቅ በዓለም አቀፍ በባዝል፣በስቶክሆልም ወይም በሮተርዳም ስምምነት መሠረት ከአካባቢና ከጤና አንፀር ጥቅም ላይ እንዳይዉሉ የተገደ ወይም በጥብቅ ገደብ የተጣለባቸዉ ቅሪታቸዉ ለረጅም ጊዜ የመቆየት ኃይል ያላቸዉና በሰዉ፣በእንስሳትና በአከባቢ ላይ በጣም አደገኛ ጉዳት የሚያደርሱና ምንጫቸዉ የማይተወቁ Persistent Organic Pollutants (እንደ ኦርጋኖ ክሎሪንና ኦርጋኖ ፎስፎረስ፡- Aldrin, Chlordane, Dieldrin, Endrin, DDT, Heptachor, Mire, Dioxin,Furans, Paraquate እና ሌሎች የመሳሰሉት አደገኛ ፀረ-ተባይን) ሳይጨምር ለግል ጥቅሙ የሚያዉል አነስተኛ መጠን ካልሆነ በስተቀር፡-

1. ከሰዉ ጋር በአንድ መጓጓዣ ክፍል ዉስጥ፣ በህዝብ ማመላለሻ፣በጭነት ተሽከረርካሪዎችና በሌሎች ማጓጓዥዎች፣ ከእንስሳቶች፣ ከምግብ፣ ከመኖ፣ ከመድሃኒቶች፣ ከአሻንጉልቶች፣ ከልብሶች፣ ከኮስሞቲክሶች፣ ከቤት ዉስጥ እቃዎች ወይም ቢበከሉ አደጋ ሊያደርሱ ወይም ሊያስከትሉ ከሚችሉ ሌሎች ነገሮች ጋር ማጓጓዝ አይቻልም፣
2. ፀረ-ተባይ ይዞ የነበረ ባዶ መያዣ የሚያጓጉዝ ማንኛዉም ሰዉ ከማንኛዉም ምግብ፣መኖ ወይም እንስሳት በመለየትና ከነዚህ ጋር እንዳይነካካ አድርጎ ማጓጓዝ አለበት፣

3. ፀረ-ተባይ የሚያንጉዝ ማጓጓዣ በፀረ-ተባይ ፍሳሽ ከተበከለ የማጓጓዙን ስራን እንዲሰራ በአዘዘዉ/ ኃላፊነት በሰጠዉ ባለሙያ ከብክለት ነፃ እንዲሆንና እንዲፀዳ ይደረጋል፣
4. የፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ፍቃድ ከተሰጠዉ ግለሰብ፣ድርጅት ወይም ማህበራት በስተቀር ከአንድ /1/ ኪሎ ግራም ወይም ሊትር በላይ ፀረ-ተባይ በክልሉ ይዞ መንቀሳቀስ የተከለከለ ሲሆን ከዚህ በላይ ይዞ የተገኘ ማንኛዉም ሰዉ በዚህ መመሪያ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፣
5. በክልሉ ዉስጥ እርሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች በራሳቸዉ ማሳ ወይም ይዞታ ላይ ለመጠቀም ሲፈልጉ ከላይ በአንቀጽ 4፣ንዑስ አንቀጽ 4.1 ፣4.2፣4.3፣4.4 የተጠቀሱትን ያሟሉ መሆኑን በዘርፉ ባለሙያዎች የተረጋገጠና በቂ መረጃን ሲያቀረብ ብቻ ግብርና ቢሮ ወይም በሚመለከታቸዉ አግባብ ባላቸዉ በየደረጃ ባሉ መዋቅር ለግሉ የሚበቃዉን ብቻ እንዲያቀርብና በዚህ መመሪያ መሠረት እንዲጠቀም ፍቃድ ሲሰጥ ብቻ ነዉ፣
6. ሆኖም የግል ባለሀብቱ ያቀረበዉን ፀረ-ተባይ ይህን መመሪያ በሚፃረር መልኩ የተጠቀመ፣አሳልፎ ለሌላ አካል የሰጠ፣ያለቦታ ያከማቸና የሰዉነት መከላከያ ትጥቅና የአጠቃቀም መመሪያ ሳያቀርብ በሰዉ ጤና፣በእንስሳትና በአከባቢ ላይ ጉዳት ያደረሰ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ ሰ መሠረት በወንጀል በህግ ተጠያቂ ይሆናል፣
7. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተጠቀሰዉ መጠን ከገበያ ወይም ሽያጭ ቦታ ወደ ቤት፣ከቤት ወደ እርሻ ቦታ እንዲሁም ከእርሻ ቦታ ወደ ሌላ እርሻ ቦታ በአርሶ አደሮችና ሌሎች ፀረ-ተባይ ተጠቃሚዎች የሚያደርጉትን መዘዋወርን ወይም እንቅስቃሰን አያጠቃልልም፣
8. ከተጠቀሰዉ መጠን በላይ ይዞ ተንቀሳቅሶ የተገኘ ማንኛዉም ሰዉ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት አዋጅ ቁጥር 674/2002 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሠረት በህግ ይወረሳል።
9. የክልሉ ግብርና ቢሮ ከግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የተወረሰዉን ፀረ-ተባይ በክልሉ አገልግሎት ላይ እንዲዉል ያደርጋል።

# ክፍል አምስት

## ተቆጣጣሪዎችን ስለመመደብ፣ተግባርና ኃላፊነት

**አንቀጽ 8 ተቆጣጣሪዎችን ወይም እንስፔክተሮችን ስለመመደብ፡-**

በክልሉ በገጠርም ሆነ ከተማ አስተዳደር በእያንዳንዱ ቀበሌ በህግ-ወጥ መንገድ ፀረ-ተባይ የሚሸጡና የሚጠቀሙት ግለሰቦች፣ድርጅቶችና ማህበራትን በመከታተል ለህግ አስከባሪ አካላት ሪፖርት የሚያቀርቡና በህጋዊ መንገድ ፍቃድ አዉጥተዉ የሚሰሩትን በአግባቡ መስራታቸዉ የሚቆጣጠር የክልል ግብርና ቢሮ በየደረጃዉ ባሉ መዋቅሮቹ ማለትም በክልል፣ዞኖችና ወረዳዎች ተቆጣጠሪዎችን ይመድባቸዋል ወይም የሰብል ጥበቃ ባለሙያዎችን ደርበዉ እንዲሠሩ ዉክልና ሊሰጣቸዉ ይችላል፡፡

## 8.1 የተቆጣጠሪዎችን /ኢንስፔክተሮች/ ተግባር

ሀ/ በክልሉ ግብርና ቢሮ በየደረጃ ባሉ መዋቅሮች በተቆጣጠሪነት ወይም ኢንስፔክቴሮች ላይ የተመደቡ ወይም ዉክልና የተሰጣቸዉ ባለሙያዎች መታወቂያቸዉን ወይም ሥራ ትዕዛዛቸዉን በማሳየት አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ፀረ-ተባይ የሚሸጡና የሚጠቀሙ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት የፀረ-ተባይ አያያዝና አጠቃቀም መረጃን በማሰባሰብ የቁጥጥሩን ስራ ያካሄዳሉ፣

ለ/ የፀረ-ተባይ ተቆጣጠሪዎች ወይም ኢንስፔክተሮች በተሰጣቸዉ ሥልጣን መሠረት ስራቸዉን በሚያከናዉኑበት ወቅት ቁጥጥሩን በሚያካሄዱበት ማንኛዉም ግለሰቦች፣ድርጅቶችና ማህበራት በተጠየቁ ጊዜ ለሥራ የታዘዙበትን ወረቀት ወይም የቢሮ መታወቂያ ማሳየት አለባቸዉ፣

ሐ/ በዚህ መመሪያ መሠረት ማንኛዉም የፀረ-ተባይ ተቆጣጠሪዎች ወይም ኢንስፔክተሮች የቁጥጥር ተግባሩን በሚያከናዉንበት ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአካባቢ ያሉ የጉምሩክ ወይም የፖሊስ ባልደረቦችን እርዳታ መጠየቅና የወጣ አዋጅ፣ መመሪያና ሌሎች የቁጥጥር፣የክትትልና የቅኝት ስራዎችን የማከናወን ስልጣን አላቸዉ፡፡

## 8.2 የፀረ-ተባይ ተቆጣጠሪዎች /ኢንስፔክቴሮች/ ኃላፊነት

1. ፀረ-ተባዩ ግለሰቦች፣ድርጅቶችና ማህበራትን የተመዘገበ መሆኑን ማረጋገጥ፣የጥራት ደረጃ /አክቲቭ ኢንግሪዲየንት/ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ምርመራ ለማካሄድ ናሙና በመዉሰድ እንዲመረመር ማድረግ፣

2. በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት አስፈላጊ ነዉ ብለዉ ላመኑባቸዉና ለተጠራጠሩባቸዉ ሌሎች ምክንያቶች ሁሉ የኬሚካል ናሙናዎችን ወስደዉ ሊያስመራምሩ ይችላሉ፣
3. ኢንስፔክተሮች መመሪያዉን ለማስፈፀም ሲባል በማናቸዉም ተገቢ በሆነ ጊዜ ይህንን መመሪያ በመጣስ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን፣ድርጅቶችን ወይም ማህበራትን መሸጫ ሱቅ ወይም ማከማቻ መጋዘኖችን በመፈተሽ ስራዉ ትክክል አለመሆኑን ሲያረጋግጡ እንቅስቃሴዉን ማገድ ይችላሉ፣
4. በዚህ መመሪያ ኢንስፔክቴሮች በተሰጣቸዉ ስልጣን መሰረት ስለእገዳ ስራዉ ለታገደበት ግለሰቦች፣ድርጅቶችና ማህበራት የፁሑፍ ማስረጃ ይሰጣሉ፣በአስራ አምስት /15/ የሥራ ቀናት ዉስጥ ተገቢዉን የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ፣
5. አግባብነት ካላቸዉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ስለፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር የወጣዉ አዋጅና መመሪያ መተግበራቸዉን ይቆጣጠራሉ፣
6. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሌለዉና የንግድ ስራ ፍቃድ የሌለዉ ግለሰብ ድርጅት፣ወይም ማህበራት ፀረ-ተባይ በየትኛዉም ቦታ ሲያዘዋዉር፣ሲሸጥ ወይም የተባይ መከላከል አገልግሎት ሲሰጥ የተገኘ ማንኛዉም ሰዉ ይዘዉ አግባብ ወዳለዉ ህግ ቦታ ያቀርባሉ፣
7. በተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ አመልካቾች አስፈላጊዉን የቴክኒክ መስፈርቶች ማሟላታቸዉን ያረጋግጣሉ፣ካረጋገጡም በኂላ ለሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት የድጋፍ ደብዳቤ እንዲፃፍ ያደርጋሉ፣የብቃት ማረጋገጫ ያሰጣሉ፣
8. በቢሮዉ ተመዝግበዉ በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩትን ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት በገቡት ዉል መሠረት እየሰሩ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ የድህረ-ምዝገባ ቅኝት ያካሄዳሉ፣በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት አዋጅ ቁጥር 674/2002 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2 አግባብነት ያላቸዉ ፍቃዶች፣መዛግብቶች ወይም ሌሎች ደጋፊ መረጃዎች እንዲቀርቡለት የመጠየቅና የመመርመር ኃላፊነት አለባቸዉ።

## ክፍል ሰድስት

### በህገ-ወጥ መንገድ የተያዘ ፀረ-ተባይ ስለመዉረስ

**አንቀጽ 9 በህገ ወጥ መንገድ የገባ፣የተከማቸና ሲዘዋወር የተያዘ ፀረ-ተባይን ስለመዉረስ፡-**

ሀ/ ማንኛዉም በፀረ-ተባይ ስራ ላይ የተሰማራ ግለሰብ፣ድርጅት ወይም ማህበራት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የንግድ ፍቃድ ሳይኖረዉ ፀረ-ተባይ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 4 ከተፈቀደ መጠን በላይ ያለፍቃድ ይዞ በክልሉ ሲንቀሳቀስ ከተያዘ፣

ለ/ በህገ-ወጥ መንገድ ክልሉ ዉስጥ ያስገባ፣ያከማቸ፣የደበቀና የፀረ-ተባዩን መለያ የለወጠ ወይም የገነጠለ፣ በመቀናነስ ባዕድ ነገር የጨመረና ዳግም ያሸገ፣በማጭበርበር የሸጠ፣ለመሸጥ የሞከረ ግለሰብ ድርጅት፣ወይም ማህበራት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት አዋጅ ቁጥር 674/2002 አንቀፅ 33 ንዑስ አንቀፅ 1፣2፣3፣4፣5 መሠረት እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ ሰ ፀረ-ተባዩ ተወርሶ ተገቢዉ ቅጣት ይወሰንበታል፣

**አንቀጽ 10 የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃቀም፡-**

ማንኛዉም ፀረ-ተባይ ተጠቃሚ በሌላ ሰዉ፣እንስሳት፣እፅዋትና አካባቢ ላይ ጉዳት በማያስከትል መልኩ መሆን ይኖርበታል። ለዚህም ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በአካባቢዉ ለሚገኙ ንብ አርቢዎች ወይም አርሶ አደሮች አስቀድሞ የማሳወቅ ግዴታ አለበት። ሳያሳዉቅ ርጭት ቢያካሄድና ጉዳት ቢደርስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ ሰ እና ሸ ጉዳት ያደረሰዉ አካል ለተጎጅዉ የካሳ ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት።

1. የንብ እርባታ በሚካሄድባቸዉ አካባቢዎች ንቦች በሚቀሳቀሱበት ሰዓት ጧት ከ12፡00 እስከ 4፡00፣ ከሰዓት ከ9፡00 እስከ 12፡00 ላይ ፀረ-ተባይ መርጨት ተከላከለ ሲሆን ይህ ሳይሆንና ሰዓቱን ሳይጠብቅ ሆን ብሎ በቸልተኝነት ንቦች በሚቀሳቀሱበት ሰዓት ጧትና ማታ የርጭት ስራ ያካሄደ ግለሰብ ወይም ድርጅት በዚህ መመሪያ በወንጀል ህጉ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፣
2. ንቦች በከፍተኛ ሁኔታ በሚራቡበት ወቅት /Swarming time/ ከመስከረም እስከ ጥቅምት እና ሚያዚያ ወር/ አበባን ከሚቀስሙበት ቦታ እንዲሁም ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንጽ 4.4 /ሠ/ ላይ የተጠቀሱትን ከሁለት /2/ ኪሎ ሜትር ባነሰ ርቀት ላይ ፀረ-ተባይ ርጭት ማካሄድ በፍፁም የተከለከለ ሲሆን ፈጽሞ የተገኘ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 መሠረት ላደረሰዉ ጉዳት የጉዳት ካሳ የመክፈል ግዴታ አለበት፣
3. ለሰዉ ጤና አደገኛ፣ሽታዉ ለረጅም ጊዜ የሚቆይና ጉዳት የሚያስከትል (ኦርጋኖ ክሎሪንና ኦርጋኖ ፎስፎረስ) ፀረ-ተባይ በአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች/ ምግብ

ቤቶች፣አልጋ ቤቶች፣መድሃኒት ቤቶች፣መጠጥ ቤቶች፣መኖሪያና ትምህርት ቤቶች ዉስጥ መጠቀም የተከለከለ ነዉ፣

4. ድርጅቱ፣ግለሰቡ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎል ስራ ላይ የተሠማራ ማህበራት አገልግሎት ሲሰጥ ለሚደረሰዉ ብክለት የሚያፀዳ ሲሆን፣ሙሉ በሙሉ ድርጅቱ ሰዉን ከሚጎዳ የፀዳና ጉዳት የማያደርስ መሆኑ በዘርፉ ባለሙያ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ፣
5. ይህንን መመሪያ የተላላፈ አካል/ድርጅት ወዲያዉኑ ታግዶ ጉዳት ለደረሰበት አካል የካሳ ክፍያና ሙሉ ህክምና ወጪዉን የሚሸፍን ይሆናል፣
6. ድርጅቱ፣ግለሰቡ ወይም ፀረ-ተባይ መከላከል አገልግሎት ሰጪዉ በአካባቢዉና በሰዉ ላይ ጉዳት ከአደረሰ ድርጅቱ ተዘግቶ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት አዋጅ ቁጥር 674/2002 አንቀፅ 33 ንዑስ አንቀፅ 1፣2፣3፣4፣5፣ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሠረት ፀረ-ተባዩ ተወርሶ ተገቢዉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ ሰ መሠረት ቅጣት ይወሰንበታል፣የተበከለዉን አከባቢ ለማጽዳት የሚያስፈልገዉን ወጪ እንዲሸፍን ይደረጋል፣
7. የብቃት ማረጋገጫ የሌለዉና በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰብ፣ድርጅት ወይም ማህበራት ታግዶ ፀረ-ተባዩ በመንግስት ይወረስና ንብረቱ ለባለቤቱ ተመላሽ ይሆናል። የተወረሰዉ ፀረ-ተባይ ሳይበላሽ የክልሉ ግብርና ቢሮ በወረርሽኝና መደበኛ ለሚከሰቱ ተባይ መከላከል አገልግሎት ላይ ያዉላል ወይም በግዥ መመሪያ መሠረት ተሸጦ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፣
8. በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት ፀረ-ተባዩን ሽያጭ ለማስፋፋት ወይም ጥቅሙን ለማስተዋወቅ በሰርቶ ማሣያ፣በስጦታ ወይም በብሮሸር ቢሮዉን አስፈቅደዉ ለሚመለከታቸዉ ተጠቃሚ ማሠራጨት ይችላሉ፣ሆኖም ቢሮዉን ሳያስፈቅዱ ወደ ተጠቃሚዉ ከአደረሱና ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፣
9. ማንኛዉም ፀረ-ተባይ ተጠቃሚ አርሶ አደሮችም ሆኑ በክልሉ ዉስጥ እርሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ከራሳቸዉ ይዞታ ወይም ከራሳቸዉ እርሻ ማሳቸዉ ዉጭ ባልተፈቀደላቸዉ ቦታዎች፣በተፈጥሮ ደኖች፣የዉል ግጦሽ መሬቶችና እንስሳት በሚዉሉበት አካባቢ ወይም ወንዝ ዳር ፀረ-ተባይን የተጠቀመና በሰዉ፣እንስሳት፣አከባቢና

በብዝሃ ሕይወት ላይ ጉዳት ያደረሰ፣በኢ.ፌ.ዴ.ራ.ል መንግስት አዋጅ 674/2002 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ ሰ መሠረት በወንጀል በህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

10. በዚህ መመሪያ ፀረ-ተባይ በነባርና አካባቢ ዕዉቀት ከእፅዋት አካላት በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጁትና ለተባይ መከላከያነት የሚጠቀሙትን ቢሮዉ ያበረታታል፤ይደግፋል፣
11. ይህ መመሪያ በብዝሃ ሕይወት እየተባዛ ያለዉ ባህላዊ የፀረ-ሰብል ተባይ መከላከያ እፅዋቶችን ያበረታታል፤ይደግፋል፣
12. በዚህ ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት ፀረ-ተባዩን ለሚሸጡት ተጠቃሚዎች ቅድሚያ ስለአጠቃቀሙ ግንዛቤ መስጠት ግዴታ አለባቸዉ፡፡

## ክፍል ሰባት

### የሙያ ድጋፍ ስለመስጠት

**አንቀጽ 11 የሙያ ድጋፍ ስለመስጠት፡-**

በክልሉ ግብርና ቢሮ በየደረጃ የተመደቡ ኢንስፔክተሮች ወይም የሰብል ጥበቃ ባለሙያዎች የቅርብ ክትትልና የሙያ ድጋፍ ለፀረ-ተባይ ተጠቃሚዎች የመስጠት ግደታ አለባቸዉ፡-

ሀ/ የዞን ግብርና መምሪያ ባለሙያዎች /ኢንስፔክተሮች በተለይም የሰብል ጥበቃ ባለሙያዎች በዚህ ስራ ዘርፍ ለተሰማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት የሙያ ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለባቸዉ፣

ለ/ የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ግብርና ጽ/ቤት ባለሙያዎች /ኢንስፔክተሮች በተለይም የሰብል ጥበቃ ባለሙያዎች በዚህ ስራ ዘርፍ ለተሠማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት የሙያ ድጋፍና የቅርብ ክትትል ማድረግ ግዴታ አለባቸዉ፣

ሐ/ የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሰብል ልማት ባለሙያዎች ወይም ልማት ጣቢያ ባለሙያዎች በዚህ ስራ ለተሰማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት የሙያ ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለባቸዉ፣

መ/ ማንኛዉም አርሶ አደር ፀረ-ተባይን ለመግዛትና ለመጠቀም ሲፈልግ በባለሙያዎች ምክረ ሃሳብ ድጋፍ የተጋዘ መሆን ይኖርበታል፤በየደረጃ ያሉ የግብርና ባለሙያዎችም ከፀረ-ተባይ ልየታና ግዥ እስከ አጠቃቀም እስክባቁ ድረስ ለአርሶ አደሩ በቅርበት የሙያና የምክረ ሃሳብ ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለባቸዉ፣

ሠ/ ከላይ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ መ ላይ የተገለጸዉን ባለሙያዉ ባለማድረጉ በቸልተኝነት በሰዉ፣ በእንስሳት ጤና፣በአካባቢና በብዝሃ ሕይወት ላይ በፀረ-ተባይ ለሚደርሰዉ ጉዳት ባለሙያዉ በክልሉ ፐብሊክ ሰርቨስና ሰዉ ሀብት ልማት ሠራተኞች አስተዳደር መመሪያ መሠረት በሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለትና እንዲሁም እንደጉዳቱ መጠን፣ሁኔታና አይነት በዚህ አንቀጽ 14 በወንጀል በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 12 ፀረ-ተባይን ማስወገድ፡-**

ሀ/ ማንኛዉም በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ሥራ ላይ የተሠማራ ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም ማህበራት የፀረ-ተባይ መጠቀሚያ ዕቃ ወይም ቆሻሻን የሰዉንና የእንስሳትን ጤና ወይም አካባቢን በሚጎዳ ሁኔታ ባልተፈቀደለት ቦታ ማስወገድ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት አዋጅ ቁጥር 674/2002 በአንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በዚህ መመሪያ ቁጥር 14 ንዑስ አንቀጽ ሰ እና ሸ መሠረት በህግ ይጠየቃል፣

ለ/ በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት በክልሉ ዉስጥ አስገብተዉ ባለመሸጥ፣ባለማሠራጨትና ከቆይታ አንፃር ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉትን ፀረ-ተባይ በወቅቱ በራሳቸዉ ወጪ ጉዳት በማያስከትል መልኩ አንድ ቦታ በማሰባሰብ በየደረጃ ለሚመለከተዉ መ/ቤት የማሳወቅ ወይም ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸዉ፡፡

# ክፍል ስምንት

## አደጋ/ስጋትና ቅጣት

**አንቀጽ 13 አደጋ/ስጋት፡-**

ሀ/ ፀረ-ተባይ በሚጓጓዝበት፣በተከማቸበት መጋዘንና በተሸጠበት ወይም ጥቅም ላይ በዋለበት በሰዉና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ የተረዳ ማንኛዉም ሰዉ ስለደረሰና ስለሚደርስ አደጋ በየደረጃ ላሉትና አግባብ ላላቸዉ ለቢሮ፣ለዞንና ወረዳ አካላት ሳይዘገይ ማሳወቅ አለበት፣

ለ/ በሚመለከታቸዉ ኃላፊዎች ወይም አሠሪ አካላት ትዕዛዝ የአረጫጭ መመሪያን ሳይከተል፣አጠቃቀም መመሪያና የሰዉነት መከላከያ ትጥቅ ሳይቀርብለት የርጭት ተግባሩን ሲያከናዉን የነበረ እና በፀረ-ተባይ ተመርዣለሁ የሚል የግብርና ባለሙያ በየደረጃ ባሉት

የግብርና ተቋማት በአካል ቀርቦ በማመልካቻ ካመለከተ በኋላ ጥያቄ የቀረበለት አካል ግለሰቡ የደም ምርመራ እንዲያደርግና ዉጤቱን እንዲያቀርብ ያደርጋል፣

ሐ/ የግለሰቡ የደም ምርመራ ዉጤት በእርግጥ በፀረ-ተባይ መመረዙን የሚያረጋግጥ ሆኖ ከተገኘ ስራዉን ያሠራዉ አሠሪ ተቋም ወይም ግለሰብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀፅ ሠ መሠረት በህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

መ/ ባልተዘጋጁ የግብርና ምርቶች ላይ የፀረ-ተባይ ቅሪት ይመርመርልኝ ጥያቄ ቢቀርብ የክልሉ ግብርና ቢሮ ለሚመለከታችዉ አግባብ ላላቸዉ አካላት የድጋፍ ደብዳቤ ሊጽፍላቸዉ ይገባል፣

ሠ/ በግል ነጋዴዎች፣ድርጅቶች ወይም ፀረ-ተባይ መከላከል አገልግሎት ሰጪዎች የተፈፀመ እንደሆነ ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ ወጪዉን ሸፍኖ ያስመራምራል፡፡ በዉጤቱ መሠረት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት አዋጅ ቁጥር 674/2002 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 3 /ሐ/ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ ሰ እና ሸ መሠረት በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 14 ቅጣት፡-**

ሀ/ ማንኛዉም ሰዉ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና ንግድ ፍቃድ ሳይኖረዉ በፀረ-ተባይ ንግድ ወይም ተባይ መከላከል አገልግሎት ሥራ ላይ የተሠማራና ወደ ክልሉ ያስገባ፣ያሰራጨ፣ያዘዋወረና የሸጠ፣

ለ/ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸዉ፣ጥቅም ላይ የማይዉሉና ምንጫቸዉ በዉል የማይታወቁ ፀረ-ተባይ እያወቀ ለግል ጥቅም ሆን ብሎ የሸጠ፣

ሐ/ የሰዉንና የእንስሳት ጤናን ወይም አካባቢን በሚጎዳ በዚህ መመሪያ ከተከላከሉት በሚቃረን የፀረ-ተባዩን ቆሻሻ ወይም የፀረ-ተባዩን መያዣን ያለአግባብ ያስወገደ፣

መ/ በዚህ መመሪያ ከተጠቀሱት ዉጭ ፀረ-ተባዩን ያከማቸ፣ያጠራቀመ ወይም ከተጠቀሰዉ መጠን በላይ ያጓጓዘ ወይም ይዞ የተገኘ፣

ሠ/ ለማጭበርበር ሆን ብሎ ከፀረ-ተባዩ መያዣ ላይ መለያ የገነጠለ፣የለጠፈ ወይም ሌላ ባዕድ የጨመረ፣እያቀናነሰ ዳግም ያሸገና ለሽያጭ ያዘጋጀ፣

ረ/ በሰዉና እንስሳት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ላይ ጥፋት ወይም ጉዳት ሊያደርስ ወይም ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ መረጃን የደበቀ፣

ሰ/ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት አዋጅ ቁጥር 674/2002 በዚህ መመሪያ በወንጀል ህግ በበለጠ ቅጣት የሚያስከትል ካልሆነ በስተቀር ከአምስት /5/ እስከ አስር /10/ ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር ሃያ አምስት ሺህ /25,000/ እስከ ሃምሳ ሺህ /50,000/ ብር ይቀጣል።

ቀ/ የፀረ-ተባይ ተቆጣጠሪዎች መረጃ ሲጠይቁ ለመተባበር ፍቃደኛ ያልሆነ፣

በ/ ሆን ብሎ በፀረ-ተባይ ተቆጣጠሪዎች የታሸገን መጋዘን ወይም መሸጫ ሱቅ የከፈተ፣

ሸ/ የመከላከያ ትጥቅ ሳያቀርብና ስልጠና ሳይሰጥ ሠረተኛዉን ፀረ-ተባይ ስራ ላይ ያሰማራ አካል፣የመንግስት ተቋም፣ግለሰብ፣ድርጅት ወይም ማህበራት በወንጀል ህግ በበለጠ ቅጣት የሚያስከትል ካልሆነ በስተቀር እስከ አምስት /5/ ዓመት በሚደርስ እስራትና ከአስር ሺህ /10,000/ ብር እስከ ሰላሳ ሺህ /30,000/ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፣ሌሎች ዉሳኔዎች እንደጥፋቱ መጠን በፍርድ ቤት የሚወሰን ይሆናል፣

ቸ/ በክልሉ ግብርና ቢሮ የሚመደቡ በየደረጃ ያሉ ተቆጣጣሪያዎች ወይም የሰብል ጥበቃ ባለሙያዎች ለግል ወይም ለድርጅቱ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በፀረ-ተባይ ንግድ ስራ ላይ ከተሠማሩ ግለሰቦች፣ድርጅቶች ወይም ማህበራት ጋር የተመሳጠረ፣የተደራደረ፣የተሳሳተ መረጃን የሰጠ /የሞላ/፣መረጃን የደበቀ፣የዋሸ፣ወይም እንዲያገኝ ያደረገ፣በኪራይ ሰብሰቢነት አስተሳሰብና ተግባር ዉስጥ የገባ ወይም እንዲገቡ የገፋፋ በክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስና ሰዉ ሀብት ልማት በሠራተኞች አስተዳደር መመሪያ በሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ተጠያቂ ይሆናል፤እንዲሁም እንደጉዳቱ መጠን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት በአዋጅ ቁጥር 674/2002 አንቀጽ 33 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ ሰ እና ሸ መሠረት በወንጀል በህግ ተጠያቂ ይሆናል።

## ክፍል ዘጠኝ

### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 15 ባለድርሻ አካላትና የመተባበር ግዴታ፡-**

በዚህ መመሪያ መሠረት ኢንስፔክተሮች ተግባራቸዉን ለማከናወን እንዲችሉ የሚመለከታቸዉ አግባብ ያላቸዉ ባለድርሻ የመንግስት ተቋማት የክልሉ ንግድ፣ትራስፖርትና ኢንዳስትሪ ልማት ቢሮ፣ፍትህ ቢሮ፣ጤና ጥበቃ ቢሮ፣አካባቢ ደንና መሬት አስተዳደር ቢሮ፣ሠራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት፣በክልሉ ያሉ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ፖሊስ አባላት፣በየደረጃ ያሉ አስተዳደር አካላት፣ሌሎች በስራ ዘርፉ የተሰማሩ ግለሰቦች፣የግል ድርጅቶችና ማህበራት የመተባበር ግዴታ አለባቸዉ፣

በየደረጃዉ ያሉ ኢንስፔክተሮች/ተቆጣጠሪዎች ወይም የሰብል ጥበቃ ባለሙያዎች ሪፖርትና ሌሎችም ጥቆማ ሲቀርብላቸዉ በየደረጃ ያሉ ኃላፊዎች ፈጣን ምላሽ መስጠትና የመተባበር ግዴታ ያለባቸዉ ሲሆን ሆን ብሎ ዉሳኔዉ በመዘገየት ምክንያት በገንዘብና በንብረት ላይ ለሚደርሰዉ ብክለትና ጉዳት በዚህ መመሪያ በህጉ መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 16 የተሻሩ መመሪያዎች፡-**

በክልሉ ግብርና ቢሮ ከዚህ በፊት ለፀረ-ተባይ ምዝገባ ፍቃድ አገልግሎት ይሰጥበት የነበረ መመሪያና ሌሎች ማንኛቸዉም ልማዳዊ የአሠራር ልምዶች በሚመለከት ተፈፀሚነት አይኖረዉም፡

**አንቀጽ 17 መመሪያዉን ስለማሻሻል፡-**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ሲያገኝ መመሪያዉን ማሻሻል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 18 መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ፡-**

ይህ መመሪያ በክልሉ ግብርና ቢሮ ከፀደቀ ታህሳስ 04 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አቶ ሙለታ ወምበር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ ኃላፊ

ታህሳስ 2010 ዓ.ም

አሶሳ

**<u>የዉል መግባቢያ ፎርማት</u>**

**ዉል ሰጪ ፡- ቤ/ጉ/ክ/መ/ ግብርና ቢሮ**

**አድራሻ -------------**

**ዉል ተቀባይ፡- አቶ/ወሮ/ወ/ሪት-----------**

**አድራሻ ----------------**

1. ውል ተቀባዩ በቤ/ጉ/ክ/መ በ------------ዞን------------ወረዳ-----------ከተማ--------ቀበሌ ነዋሪ የሆንኩት እኔ --------- የተረከቡት በፀረ-ተባይ ንግድ /ጅምላ አከፋፋይ/ችርቻሮ/ተባይ መከላከል አገልግሎትስራ ላይ ለመሰመራት በ------------ዞን------------ወረዳ----------- ከተማ--------ቀበሌ የፀረ-ተባይ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፍቃድን በማዉጣት በደንቡ መሠረት ለመስራት ውል ገብተዋል፡፡

2. ውል ተቀባይ በእፁዋት ጥበቃ፣በእፅዋት ሳይንስ ወይም በአጠቃላይ እርሻ በድፕሎማ የተመረቀና አራት ዓመትና በላይ፣በድግሪ ሁለት ዓመትና በላይ በሁለተኛ ድግሪ ዜሮ ዓመት የስራ ልምድ ያላቸዉን ባለሙያ ለመቅጠር ወይም የትምህርት ዝግጅት ከላቸዉ በራሳቸዉ ስራዉን በትክክል ለመስራት ውል ገብተዋል፡፡
3. የመሸጫ ሱቅና መጋዘን በግንብ የተሠራ ከመኖሪያ ቤት፣ ከገበያ ቦታዎች ከሕፃናት መዋያዎች፣ ከወንዝና ኩሬዎች ከ100 ሜትር በላይ የራቁ አዘጋጅቶ ውል ገብተዋል፡፡
4. ውል ተቀባይ በእጅ የገቡትን ፀረ-ተባዮች ዬት ቦታ እንደ ደረሱ የሚገልጽ መዝገብ ለማዘጋጀትና መረጃዎችን ለመደራጀት ዉል ገብቷል፡፡
5. ውል ተቀባይ የተከፋፈለውን መጠን ለማን እንደተከፋፈለ፣ዓይነቱን፣ መጠኑን፣የተሸጠበትን ጊዜ የተሸጠለት ድርጅት፣ወይም ግለሰብ በተዘጋጀው መዝገብ ላይ ለመመዝገብና በተጠየቁበት ጊዜ ለማሳየት ወይምበየሦስት ወሩ ሪፓርት ለማቅረብ እንዲሁም ለእድሳት ሲመጡ አጠቃላይ ሪፖርቱን ይዘዉ ለመምጣት ውል ገብተዋል፡፡
6. የ-----------ዞን ግብርና መምሪያና የ----------- ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የሰብል ጥበቃ ባለሙያዎች፣ ወይም እንስፔክተሮች የዞንና የክልሉ ግብርና ቢሮ ባለሙያዎችና እንስፔክተሮች በማንኛውም የሥራ ቀናትና ሰዓት የፀረ-ተባይ ድርጅቱን መፈተሽ፤ ከህገ ደንብ ዉጪ ሆኖ ሲያገኙና ከፍተኛ ችግር ያመጣል ብሎ ከአመኑበት የመሸጫ ሱቁን ለተወሰነ ጊዜ እንደሚያሽጉ ዉል ተስማምተዋል፡፡
7. የክልሉ ግብርና ቢሮ ፀረ-ተባዮን በሚመለከት በየጊዜው የሚወጡትን ሕጎች፣ ደንብና መመሪያ ለማክበር ውል ገብተዋል፡፡
8. የፀረ-ተባይ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፍቃድ በየዓመቱ የሚታደስ ሆኖ የክልሉ ግብርና ቢሮ ለክልሉ ንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፓርት ልማት ቢሮ ወይም ለዞን ወይም ለወረዳ ንግድ፣ኢንዱስትሪና ትራንስፓርት መምሪያ /ለዞን/ ለወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት በሚፃፍ የድጋፍ ደብዳቤ ብቻ ለማሳደስ ዉል ገብቷል፡፡
9. የፀረ ተባዮን መሸጫ ሱቅ ወይም መጋዘን ለክልሉ ግብርና ቢሮ ሳያውቅ ወደ ሌላ ቦታ ላለማዛወር ዉል ገብቷል፡፡
10. በየደረጃ ያሉ ሰብል ጥበቃ ባለሙያዎች ወይም እንስፔክተሮች የታገዱ፣ያልተመዘገበና የአገልግሎት ጊዜዉ ያለፈበት ፀረ-ተባይ ሲሸጥ ከተገኙ ወይም ከደንብና መመሪያ ውጭ ሲሸጥ ከተገኙ ለሕግ አቅርቦ የማስቀጣትና ለንግድ፣ ኢንዱስትሪና ትራንስፓርት ልማት ቢሮ በማሳወቅ ንግድ ፍቃዱን እስከ ማሰረዝ መብት አላቸው፡፡

11. ድርጅቱ ወይም ግለሰቡ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ለቢሮዉ ሳያሳዉቀዉ በሌላ ሰው ስም ላለማዛወር ዉል ገብቷል፡፡
12. ይህ ውል ከ------ ዓ.ም እስከ ----- ዓ.ም የፀና ሆኖ እንደገና ይታደሳል፡፡

**ውሉን ያዘጋጀዉ**

ስም-------------------------------

ፊርማ -----------------------------

ማዕረግ-----------------------------

ቀን------------------------------------

**ዉሉን ያረጋገጠዉ**

ስም-----------------------------------

ፊርማ------------------------------

ማዕረግ-------------------------------

ቀን-----------------------------------

**ዉል ሰጪ**

ስም -------------------------
ፊርማ-------------------------
ማዕረግ------------------------
ቀን-----------------------------

**እማኞች**

| ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| 1ኛ--------------- | ------------- | -------- |
| 2ኛ-------------- | -------------- | -------- |
| 3ኛ---------------- | ------------ | ------ |

**ዉል ተቀባይ**

ስም-------------------------

ፊርማ----------------------

ማዕረግ------------------------

ቀን-----------------------------

**ዉሉን ያፀደቀዉ**

ስም--------------
ፊርማ------------
ማዕረግ------------
ቀን------------------

**በፀረ - ተባይ ንግድ ስራ ላይ ለሚሠማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሚሞሉአቸው መስፈርቶች (በወረዳ ባለሙያ የሚሞላ)**

1. የፈቃድ ዓይነት -----------------------------------------------------------------------------
2. የአመልካች ስም ----------------------------------------------------------------------------
3. አድራሻ፣ቤ/ጉ/ክ ----ዞን ----ወረዳ -----ከተማ -----ቀበሌ ------የቤት ቁጥር ----ስልክ ቁጥር --
   3.1 የተቀጠረ የባለሙያ ስም ---------------------------- ሥራ -----------------------------------
   3.2 አድራሻ ------ከተማ -------ወረዳ ------ቀበሌ ----የቤት ቁጥር -----ስልክ ቁጥር ----------
   3.3 የትምህርት ደረጃ ---------------------------- የትምህርት ዓይነት ----------------------------
   3.4 የአገልግሎት ዘመን ጠቅላላ ----------በሰብል ጥበቃ/ሰብል ልማት ----------------
   3.5 የቅጥር ውል ሁኔታ ------------------ ቅጥሩ የሚቆዩበት ጊዜ -----------------------------
4. የመጋዘን ሁኔታ
   4.1 አድራሻ ከተማ ------------- ወረዳ --------------- ቀበሌ ------------- የቤት ቁ.-----------
   4.2 የመጋዘን ስፋት --------------------- ሜ.ካሬ -----------------፣ በሮች ብዛት -----------

4.3 ወለሉ ---------------------------------------

4.4 መስኮቶች ብዛት ----------------------------- ስፋት ----------------------

4.5 ጣሪያው ርዝመት --------------------------- ሜትር ---------------------

4.6 የገላ መታጠቢያ --------------------መፀዳጃ ቤት-------------- ውሃ ---------- መብራት --

4.7 የእሣት አደጋ መላከል ብዛት ------------------- የሚሠራ -------------- የማይሠራ -------

4.8 የአጥር ግቢው ስፋት ------------------- ለብቻው የተከለለ ነው ----------------- አይደለም

5. መከላከያ ትጥቅ ዓይነትና ብዛት፡- ቱታ -------ቦት ጫማ -------ጓንት --------የዓይን መነጽር -----ማስክ የአቧራ -------- የጋዝ -----------------------

6. የመረጃ አያያዝ

6.1 መዝገብ አለ ------------------------- የለም ---------------------

6.2 የተሸጠውን ዓይነት ያሣያል ------------------- አያሣይም ---------------------

6.3 የተሸጠውን መጠን ያሳያል -------------------- አያሣይም ---------------------

6.4 የተሸጠውን ቀን ያሳያል ----------------------- አያሳይም ----------------------

6.5 የተሸጠለትን ግለሰብ ወይም ድርጅት ያሳያል ------------------ አያሳይም ------------

6.6 በጥቅም ላይ የዋለው መጠንና ዓይነት ያሳያል ---------------- አያሳይም -------------

7. ድርጅቱ ከቤት የሚሸጣቸው ወይም በመጋዘኑ የሚያከማቻቸው ሌሎች ቁሳቁሶች ካሉ

7.1 የሰው መድሃኒት አለ ------------------------ የለም ---------------------

7.2 የእንስሳት መድሃኒት አለ -------------------- የለም ----------------------

7.3 የምግብ መድሃኒት አለ --------------------- የለም ----------------------

7.4 ሌሎች ቁሳቁሶች አለ ------------------------- የለም -----------------------

8. በፀረ-ተባይ ስራ የሚሠማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በተጨማሪ የሚያሟሏቸው ቁሳቁሶች

8.1 የተዘጋጀ የመርጫ መሣሪያ ዓይነትና ብዛት
ናፕሣክ ---------------------- የሚሠራ ---------------------የማይሠራ -----------------
ማቀነናሻ-------------------- የሚሠራ -------------------- የሚሠራ --------------------

8.2 የተዘጋጀ ጋዝ ማጠጫ ሽራ መለጠፊያ ኘላስተር ---------------------ሌሎች-------

8.3 የእጅ መሣሪያዎች መፍቻ -----------መቆራረጫ ---------ሌሎች ካሉ --------------

9. ምርመራውን ያከናወኑት ባለሙያዎች አስተያየት ----------------------------------------------

10. የተቆጣጠሪዎች/ኢንስፔክተሮች ሙሉ ስምና ኃላፊነት፣ ----------------------------------------

| ስም | የኃላፊነት ደረጃ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| 1. --------------------------- | --------------------- -- | --------------------- | ----------------- |

2. ---------------------------- ---------------------- -- ---------------------- --- -------
3. ---------------------------- ---------------------- ------------------------ ------------------------
12/ የፈቀደው ጽ/ቤት/የቅርብ ኃላፊ አስተያየት -------------------------------------------------------

| <u>ስም</u> | <u>የኃላፊነት ደረጃ</u> | <u>ፊርማ</u> | <u>ቀን</u> |
| --- | --- | --- | --- |
| -------------------------- | -------------------------- | ----------------------- | --------------- |

<u>**ማስታወሻ**</u>፡- ይህ ቅጽ የፀረ-ተባይ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በሚታደስበት ጊዜ ሁሉ ይሞላል፡፡

- ቅጹ በትክክል መሞላቱን ለማረጋገጥ ኤንስፔክተሮች እንደአስፈላጊነቱ ክትትል ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡
- ባለሙያዎች ቅጹን ሲሞሉ በትክክለኝነቱን መረጋገጥ አለባቸዉ በዉሸትና በልተረጋገጠ መረጃ ከሞሉ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
- ቅጹ የሚሞሉት ሁለት የዘርፉ ባለሙያ መሆን አለባቸዉ::